ቻርተር አዋጅ ቁጥር --------------- 2009

## የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበርን እንደገና ለማቋቋም የወጣቻርተር አዋጅ

የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴ አካል የሆነው የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበርበዘር፣ በቀለም፣ በዜግነት፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ልዩነት ሳያደርግ በጦር ሜዳ ለሚቆስሉና ለሚጐዱ በአጠቃላይ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ለሚጠቁ ሰዎች ተፈላጊውን ሰብዓዊ ዕርዳታ በፍጥነት የሚሰጥና በሰዎች ዘንድ መግባባት፣ መተባበር፣ ወዳጅነትና ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የሚጥር በመሆኑ፤

ማኅበሩ በ1927 ዓ.ም ተመስርቶ በዚሁ ዓመት በአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ እውቅና አግኝቶ የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ፌዴሬሽንአባል በመሆን በመንግሥትና በኅብረተሰቡ በተለይም በአባላቱ ጠንካራ ድጋፍ በመዋቅር ስፋትም ሆነ በአገልግሎት አቅርቦት እያደገ መምጣቱን በመገንዘብ፤

ማኅበሩ በጦርነት ጊዜ በአንድም ሆነ በሌላ ሁኔታ በጦርነቱ ጉዳት ላይ የወደቁትን እና በአደጋዎች ለተጐዱ ሰዎች እርዳታ ከማቅረቡም በተጨማሪ በሃገሪቱ የልማት ሥራዎች ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የሚያደርገው ተሳትፎ እንዲሁም ዝቅተኛ የሆነው የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ በአነስተኛና በመሠረታዊ መመዘኛዎች ተቀባይነት ወዳለው ደረጃ ለማሸጋገር ለሚደረገው ጥረት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ሊበረታታ የሚገባው በመሆኑ፤

ከአካባቢያዊ አየር ሚዛን መናጋትና ከተፈጥሮ ሃብቶች መራቆት ጋር በተዛመደ መልክ የሚከሰቱትን የድርቅና የረሃብ አደጋዎች በመከላከሉ ጥረት የሚያደርገው አስተዋጽኦ ተገቢና አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ማኅበሩ አላማውንና ተልዕኮውን ለማሳካት እንዲሁም የሚጠበቅበትን ሰብዓዊ አገልግሎት በብቃት ለማከናወን እና ራሱን ለመቻል የተለያዩ የገቢ ምንጮችን ለማፍራት የሚያደርገውን ጥረት ከግቡ ለማድረስ እና እየተገበረው ያለውን የለውጥ ሂደት በስኬት ለመፈጸም ቀልጣፋ፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን አወቃቀር እና አደረጃጀት መከተል ያለበት በመሆኑ፤

የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ የማኅበሩ ቻርተር እንደገና እንዲሻሻል ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበርን እንደገና ማቋቋሚያቻርተር አዋጅ ቁጥር ----------/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ ቻርተር አዋጅ ውስጥ፤

1/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ክልል ሲሆን፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደርን ይጨምራል፤

2/ "የቀይ መስቀል ወጣት" ማለት ዕድሜው ከ15 ዓመት እስከ 30 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ወጣት አባል ነው፤

3/ "እንቅስቃሴው" ማለት ብሔራዊ የቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ማኅበራትን፤ ዓለም አቀፉን የቀይ መስቀል ኮሚቴ እና ዓለም አቀፉን የቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ፌዴሬሽንን በአባልነት የያዘ ጥምረት ነው፤

4/ "በጎ ፈቃደኛ" ማለት በራሱ ተነሳሽነት ያለምንም ጥቅም ፍለጋ እንዲሁም ያለ አንዳች ውጫዊ ተጽዕኖ ማኅበሩ በሚያካሂደው ሰብዓዊና የልማት ተግባራት የሚሳተፍ ሰው ነው፤

5/ "የጄኔቫ ስምምነቶች" ማለት ነሐሴ 06 ቀን 1941 የተፈረሙት የጄኔቫ ስምምነቶችና ሰኔ 01 ቀን 1969 የተፈረሙት ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች ናቸው፤

6/ "የድርጅት አባል" ማለት በማኅበሩ የተወሰነውን የገንዘብ መዋጮ የሚከፍል እና የአባልነት ግዴታዎቹን የሚወጣ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማንኛውም ድርጅት ሲሆን ይህም የግል፣የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና አለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ኤምባሲዎችን እና ተቋማትን ያጠቃልላል፤

7/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

8/ በዚህ ቻርተር ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. <u>የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር</u>

1/ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር (ከዚህ በኋላ ማኅበሩ እየተባለ የሚጠራ)የሕግ ሰውነት ያለው ለትርፍ ያልተቋቋመ ሀገር አቀፍ የቀይ መስቀል ማኅበር ሲሆን የሰብዓዊ ተግባሩንም በሁሉም የኢትዮጵያ ግዛት ወሰን ያዳርሳል፡፡

2/ ማኅበሩየተቋቋመበትን ተግባርበዚህ ቻርተር፣ በጀኔቫ ስምምነቶች፣ በእንቅስቃሴው መተዳደሪያ ደንብ፤ እንቅስቃሴው በሚያደርገው ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች እና በልዑካን ምክር ቤት በሚተላለፉ ውሳኔዎች እና በዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ፌደሬሽን ማቋቋሚያ ደንብ መሠረት ተግባሩን ያከናውናል፡፡

## 4. <u>የማኅበሩ ዓርማ</u>

የማኅበሩ ዓርማ በነጭ መደብ ላይ በጉልህ የሚታይ ቀይ መስቀል ሲሆን የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበርየሚል ጽሁፍ በሙሉ ወይም በምህጻረ ቃል የተጻፈ ይኖረዋል፡፡

## 5. <u>ስለዓርማው አጠቃቀም</u>

1/ የዓርማው አጠቃቀም በጄኔቫ ስምምነቶች፣ ብሔራዊ ማኅበራት በአርማው የሚጠቀሙበትን ሁኔታ በሚመለከት በ1984 ዓ.ም በእንቅስቃሴው አለምአቀፍ ስብሰባ በተደነገገው ደንብ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው የሃገሪቱ ህጎች መሠረት የተወሰነ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንም ሰው ያለ ማኅበሩ ፈቃድ እና እውቅና አርማውን በማንኛውም ሁኔታ መጠቀም አይችልም፡፡

3/ የማኅበሩአባላት፣ ሰራተኞቹ እንዲሁም የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች አርማውን ስለሚጠቀሙበት ሁኔታ እና ለአርማው መደረግ ስላለበት ጥበቃ የሚወስን የጄኔቫ ስምምነቶችን፣ ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች እና ብሔራዊ ማኅበራት በአርማው የሚጠቀሙበትን ሁኔታ በሚመለከት በ1984 ዓ.ም በእንቅስቃሴው ዓለም ዓቀፍ ስብሰባ በተደነገገው ደንብ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሀገሪቱ ሕጎችን መሠረት ያደረገ የውስጥ ደንብ ያወጣል፡፡

4/ ማኅበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) በተገለጸው መሰረት አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር አርማው በሀገር ውስጥ ለትክክለኛ ዓላማ መዋሉን ይከታተላል፡፡

## 6. <u>መሠረታዊ መርሆች</u>

የማኅበሩ መሠረታዊ መርሆች የሚከተሉት ናቸው፤

### 1/ ሰብዓዊነት

ማኅበሩ ያለ አድልዎ በጦር ሜዳ የቆሰሉትን ለመርዳት በተፈጠረ ጽኑ ዓላማ ላይ የተቋቋመ እንደመሆኑ በአለማቀፋዊና በብሔራዊ ደረጃ ባለው አቅም ሁሉ በማናቸውም ስፍራና ጊዜ በሰዎች ላይ የሚደርሰውን ችግርና ስቃይ ለመከላከልና ለማቃለል ይጥራል፡፡ ጥረቱ ህይወትን መጠበቅ፣ ጤንነትን መንከባከብ፣ እንዲሁም የሰብዓዊ ፍጡራንን ክብር መጠበቅን ማረጋገጥ ነው፡፡ እንቅስቃሴው በህዝቦች መካከል የጋራ መግባባት፣ ወዳጅነት፣ ትብብርና ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍንም ይሰራል፡፡

### 2/ አለማዳላት

ማኅበሩ በዜግነት፣ በዘር፣ በጾታ፣በሃይማኖት፤ በመደብ ወይም በፖለቲካ አመለካከት አድልዎ አያደርግም፡፡ ጥረቱ የሰዎችን ስቃይ በፍላጎታቸው ብቻ በመመራት በጣም አስቸኳይ ዕርዳታ ለሚፈልጉ የስቃይ ሁኔታዎች ቅድሚያ መስጠት ነው፡፡

### 3/ ገለልተኝነት

የሁሉንም ወገኖች እምነት አግኝቶ ያለችግር ተግባሩን ለማከናዎን እንዲችል ማኅበሩ በማናቸውም ግጭቶችና ጦርነቶች ለማንም አይወግንም፤ እንዲሁም በማንኛውም የፖለቲካ፣ የዘር፣ የሃይማኖት ወይም የርዕዮት አለም ውዝግቦች ገለልተኛ አቋሙን ይጠብቃል፡፡

### 4/ የአሠራር ነፃነት

ማኅበሩ የአሰራር ነጻነት አለው፡፡ ማኅበሩ ለሀገሪቱ ሕግ ተገዥ እና በሰብዓዊ አገልግሎት ተግባር ለመንግስት አጋዥ ቢሆንም ምንጊዜም በእንቅስቃሴው መርሆች መሰረት ተግባሩን የማከናወን ነጻነት አለው፡፡

### 5/ የበጐ ፈቃድ አገልጋይነት

ማኅበሩ በምንም አይነት ለጥቅም ያልቆመና በበጎ ፈቃድ ብቻ ተነሳስቶ ለሰዎች እርዳታ የሚያደርግ ነው፡፡

### 6/ አንድነት

ማኅበሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቸኛው የቀይ መስቀል ማኅበር ነው፡፡ ማኅበሩ ለማንኛውም ዜጋ አባልነት ክፍት ሲሆን አገልግሎቱንም በሀገሪቱ ውስጥ በሁሉም ቦታ ማዳረስ አለበት፡፡

7/ **ዓለምአቀፋዊነት**

ማኅበሩ እኩል ደረጃ ካላቸውና እርስ በእርስ በመረዳዳት እኩል ኃላፊነትና ግዴታ ከሚጋሩ ብሔራዊ ማህበራት ጋር በመረዳዳት የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት የሚሰራ ነው።

## 7. ዓላማ

የማኅበሩ ዓላማ የጄኔቫ ስምምነቶችንና በዚህ ቻርተር አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን መሠረታዊ መርሆች በመከተል የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1/ በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ አደጋ ግጭቶችን ጨምሮ በሰው ህይወትና ጤና ላይ የሚደርሰውን ስቃይ እና መከራ ማቃለል፣ የተጠፋፉ ቤተሰቦችን ማገናኘት፣ የአደጋ ተጎጂዎች ከጉዳቱ በፍጥነት እንዲያገግሙ የማድረግ፤

2/ በተፈጥሮ አደጋ ግጭቶችን ጨምሮ በሰው ጤናና ህይወት ላይ አደጋ እንዳይደርስ መከላከል፣ የህብረተሰቡን አደጋ የመቋቋም አቅም የማዳበር፤

3/ ሰብዓዊነት፣ በጎ ፈቃደኝነት እና የሰው ልጆች ሰላም እንዲሰፍን መስራት።

## 8. ከመንግስት ጋር ስላለው ግንኙነት

1/ ማኅበሩ የተቋቋመለትን ዓላማ እና መሠረታዊ መርሆችን በመጠበቅ በሰብዓዊ ተግባራት የመንግስት አጋዥ ነው።

2/ መንግስት ማኅበሩ የተቋቋመለትን ዓላማ እንዲያሳካ እና በዚህ ቻርተር የተዘረዘሩትን ተግባራት እንዲፈጽም አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

3/ ማኅበሩ ከመንግስት አካላት ጋር ስለማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ የሚያደርጋቸው ስምምነቶች በጽሁፍ መሆን አለባቸው።

## 9. ተቋማዊ ነጻነት

1/ ማኅበሩ የተቋቋመለትን ዓላማ ሲያከናውን ተቋማዊ ነጻነት አለው።

2/ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ከማኅበሩ ጋር የሚያደርጓቸው ማናቸውም ግንኙነቶች ከማኅበሩ መርሆች ጋር የሚጻረሩ መሆን የለባቸውም።

## 10. ከሌሎች አካላት ጋር ስላለው ግንኙነት

1/ ማኅበሩ ከሌሎች የእንቅስቃሴው አካላት ጋር ስላለው ግንኙነት በእንቅስቃሴው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 3 እና 4 የተቀመጡትን ድንጋጌዎች እንዲሁም በዓለም ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ፌዴሬሽን መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8 ላይ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ያከብራል።

2/ ማኅበሩ የተቋቋመለትን ዓላማ ለማሳካት መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት፣ ህዝባዊ ማኅበራት እና አግባብነት ካላቸው የግል ድርጅቶች ጋር ሊሰራ ይችላል፡፡

## 11. <u>ተግባራትና ችሎታ</u>

ማኅበሩ የሚከተሉት ተግባራትና ችሎታ ይኖሩታል፤

1/ በትጥቅ ግጭት፣ በውስጥ አለመረጋጋቶችና ውጥረቶች፣ በድንገተኛ እና በሌሎች አደጋዎች ውስጥ የሚገኙ ተጋላጭ ሰዎችን እና የህብረተሰብ ክፍሎችን ሁኔታ ማሻሻል፤

2/ ከባድ ችግር ወይም ድንገተኛ አደጋ በደረሰ ጊዜ የተጐዱ ሰዎች አስፈላጊውን ዕርዳታ በፍጥነትና በሚገባ እንዲያገኙ ማድረግ፤

3/ በጦርነት ጊዜ ለተጐዱ የጦር አባላትም ሆነ ሰላማዊ ህዝብ በጄኔቫ ስምምነቶችና በመሠረታዊ መርሆቹ መሠረት ዕርዳታ ማድረግ፣ ለዚህም በሰላም ጊዜ ተዘጋጅቶ መገኘት፤

4/ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተፈናቀሉትን መልሶ ማቋቋምና በልማት ተግባር ላይ ተሰማርተው ራሳቸውን የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ በአደጋ ተጋላጭነት ምላሾች ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣ ከመንግስት ጋራ በመተባበር የአደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ እና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፤

5/ በሽታዎችን ለመከላከል፣ ለህዝብ የጤና አገልግሎት ለማዳረስ፣ የጤና ባለሙያዎችን ለማሰልጠን በአጠቃላይ የጤንነት ሁኔታን ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት መተባበርና መርዳት፣ የመሠረታዊ ጤና ክብካቤ ተግባራት የሚስፋፉበትን መንገድ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር መቀየስና መተግበር፤

6/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በአካባቢ ጥበቃ፣ ማኅበረሰብ ልማት ማለትም በደን ልማት፣ በንጹህ ውሃ አቅርቦት፣ በአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ ተግባራት በመሳተፍ ተገቢውን አስተዋጽኦ ማድረግ፤

7/ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ለአደጋ በቀላሉ የሚጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ በተለይም የሴቶችን፣ሕጻናትን፣ አረጋውያንንእና አካል ጉዳተኞችን ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት ከተጋላጭነት ለመውጣት የሚያደርጉትን ጥረት ማገዝ፤

8/ በሰዎች ሁሉና በሃገራት መካከል የመግባባትና የመተባበር መንፈስ እንዲዳብር ለማገዝ ለሰብዓዊ አገልግሎቶች መሠረት የሆነውን የአለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ በኅብረተሰቡ ዘንድ በስፋት እንዲታወቅ ማድረግ፣ ለህጉ ተግባራዊነት መንግስት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ማገዝ እና መደገፍ፤

9/ የእንቅስቃሴው የልዑካን ምክር ቤት በሚያወጣው ስትራቴጂ መሰረት የተጠፋፉ ቤተሰቦችን ማገናኘት፤

10/ የእንቅስቃሴው መሠረታዊ መርሆች በሕዝብ ዘንድ በይበልጥ እንዲታወቁ ጥረት ማድረግ፤

11/ አባላትንና የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎችን ማበራከት እና ማኅበሩ ለሚያከናውነው የሰብዓዊ አገልግሎት እና የልማት ተግባራት ማሰማራት፤

12/ የቀይ መስቀል ወጣቶች እንቅስቃሴ በወጣቶችና በሌላውም ኅብረተሰብ ዘንድ እንዲታወቅና እንዲስፋፋ ማድረግ፤

13/ በአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ለመስጠት የሚዘጋጁትን፣ ለኅብረተሰቡ ደኅንነት አገልግሎት የሚያበረክቱትንና ሌሎችም የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎችን በማኅበሩ ሥራ እንዲሰለጥኑና እንዲያገለግሉ ማድረግ፤

14/ ከእንቅስቃሴው አካላትና ከሌሎችም አለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር ያለውን ግንኙነት በማስፋፋትና በማጠናከር በዓለም ላይ መግባባትና ሰላም እንዲሰፍን ጥረት ማድረግ፤

15/ ከዓላማውና ተግባሩ ጋር በማይቃረን ሁኔታ ለማኅበሩ አገልግሎቶች ማስፋፊያ ቋሚ ገቢ የሚያስገኙ ልዩ ልዩ ዕቅዶችን መተለም፣ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣ ራስን ለመቻል የሚደረገውን ጥረት ማጠናከር፤

16/ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን፣ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

17/ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ማከናወን።

## ክፍል ሁለት

## ስለ አባልነት

### 12. አባል ስለመሆን

የማኅበሩን መርሆች የሚቀበልና በሥራ ለመተርጎም ፈቃደኛ የሆነ ማንኛውም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በዜግነት፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግበት አባል ሊሆን ይችላል።

### 13. የአባልነት ዓይነቶች

የአባልነት ዓይነቶች የሚከተሉትን የሚያካትት ይሆናል፤

1/ መደበኛ አባልነት፤

2/ የዕድሜ ልክ አባልነት፤

3/ የክብር አባልነት፤

4/ የድርጅት አባልነት፤

5/ የቀይ መስቀል ወጣት አባልነት።

## 14. <u>ለአባልነት የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>

1/ ለመደበኛ አባልነት የሚያበቁ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ) በብሔራዊ ጠቅላላ ጉባዔው በሚወሰነው መሠረት የዓመቱን የአባልነት ክፍያ መክፈል፣ወይም

ለ) የማኅበሩን አላማ በጠበቀ መልኩ ከአባልነት ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ንብረት ለማኅበሩ ማበርከት፣ ወይም

ሐ) ማኅበሩ የሚፈልገውን ዓይነት አገልግሎት በነፃ መስጠት፡፡

2/ ማንኛውም ግለሰብ የዕድሜ ልክ አባል ለመሆን የሚችለው በብሔራዊ ጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔ መሠረት ለዕድሜ ልክ አባልነት የሚከፈለውን ገንዘብ በአንድ ጊዜ በመክፈል ወይም የማኅበሩን አላማ በጠበቀ መልኩ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ንብረት በስጦታ መልክ በማበርከት ወይም ከክፍያው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ነፃ አገልግሎት በመስጠት ነው፡፡

3/ የክብር አባል ለመሆን የሚቻለው ከማኅበሩ መርሆች ጋር በተዛመደ ሁኔታ ከቀይ መስቀል ስራዎች እና አላማዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ሰብዓዊ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ በማበርከት ሲሆን፤ የሚፈቀደውም በብሔራዊ ጠቅላላ ጉባዔ ነው፡፡

4/ የድርጅት አባል መሆን የሚቻለው በብሔራዊ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ለድርጅት አባልነት የሚከፈለውን ዓመታዊ ክፍያ በመፈጸም ይሆናል፡፡

5/ የቀይ መስቀል ወጣት አባል መሆን የሚቻለው ማኅበሩ ውስጥ በሚቋቋሙ የወጣት ክበባት ውስጥ በአባልነት በመመዝገብ እና በብሔራዊ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ለአባልነት የሚከፈለውን አመታዊ ክፍያ በመፈጸም ነው፡፡

## 15. <u>የአባልነት መብቶች</u>

1/ ማንኛውም መደበኛ ወይም የዕድሜ ልክ አባል እንዲሁም ዕድሜው 18 ዓመት የሞላው የቀይ መስቀል ወጣት አባል፣

ሀ) በማኅበሩ የቀበሌ፣ የወረዳና ቅርንጫፉን ወክሎ በሚገኝባቸው የማኅበሩ ስብሰባዎች ላይ ለመገኘትና ድምጽ ለመስጠት፣ እና

ለ) በማናቸውም ደረጃ ከማኅበሩ መሪዎች አንዱ ሆኖ ለመመረጥ ይችላል፡፡

2/ የድርጅት አባልነትን ወክሎ በማኅበሩ ጠቅላላ ስብሰባዎች የሚገኝ ሰው ድምጽ ለመስጠት ይችላል፡፡ ሆኖም ለመመረጥ አይችልም፡፡

3/ የክብር አባል በማኅበሩ ጠቅላላ ስብሰባዎች በመገኘት ሃሳብ ለመስጠት ይችላል፡፡ ሆኖም ድምጽ ለመስጠትም ሆነ ለመመረጥ አይችልም፡፡

16. <u>አባልነት የሚሠረዝበትና የሚታደስበት ሁኔታ</u>

1/ አባልነት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሠረዝ ይችላል፤

ሀ) መደበኛ አባላትን በሚመለከት የዓመቱ የአባልነት ክፍያ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሲቋረጥ፤

ለ) አባልነቱ የተገኘው ለማኅበሩ ነፃ አገልግሎት በመስጠት ከሆነ ይኸው አገልግሎት ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሲቋረጥ፤ወይም

ሐ) አባሉ የማኅበሩን መሠረታዊ መርሆች ሲጥስ ወይም የማኅበሩን መርሆች ወይም ተግባር አደጋ ውስጥ በሚከት እንቅስቃሴ ውስጥ ሲሳተፍ፣ የማኅበሩን መልካም ስም የሚያጎድፍ ስብዕና ሲያንጸባርቅ።

2/ የዘመኑን መዋጮ በመክፈል ወይም የተቋረጠውን አገልግሎት እንደገና በመቀጠል ወይም ከክፍያው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ንብረት በመስጠት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሀ) ወይም (ለ) መሠረት የተሠረዘ አባልነትን ማደስ ይቻላል።

3/ አባልነት የሚሠረዘው እንደአግባቡ በወረዳ፣ በዞን ፣ በክልል ወይም በብሔራዊ የአስተዳደር ቦርድ ሲሆን ውሳኔውን ለማስለወጥ የሚቀርብ ይግባኝ የሚታይበት ሥርዓት በማኅበሩ የውስጥ ደንብ ይወሰናል።

4/ አንድ አባል ከአባልነቱ እንዲሰረዝ ውሳኔ ሲሰጥ ውሳኔውን ከነምክንያቱ አባሉ በጽሁፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፤ ውሳኔው ለሚመለከተው ቅርንጫፍ ቀጣይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ቀርቦ የጠቅላላ ጉባኤው አባላት እንዲያውቁት ይደረጋል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የማኅበሩ አደረጃጀትና አወቃቀር</u>

17. <u>የማኅበሩ የበላይ ጠባቂ</u>

1/ የማኅበሩ የበላይ ጠባቂ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ነው።

2/ ፕሬዚዳንቱም ማኅበሩ ዓላማውን ከግቡ እንዲያደርስ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ እንዲያገኝ፣ በሕዝብ የበለጠ እንዲታቀፍ እናአገልግሎቱ እንዲስፋፋ ድጋፍ ያደርጋል።

## 18. የማኅበሩ አደረጃጀት

1/ ማኅበሩ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ መንግስት አደረጃጀትን ተከትሎ አንድነቱን በጠበቀ መልኩ በብሔራዊ እና ክልላዊ አደረጃጀት ተደራጅቷል፡፡

2/ የክልል አደረጃጀት የክልሉን አስተዳደራዊ መዋቅር በመከተል እንደአስፈላጊነቱ የዞን/የልዩ ወረዳ፣ የወረዳ እና የቀበሌ አደረጃጀት ይኖረዋል፡፡

3/ የማኅበሩ ብሔራዊ አደረጃጀት የማኅበሩን አላማ ለማሳካት ሀገራዊ እና አለምአቀፋዊ ተግባራትንና ኃላፊነትን ያከናውናል፡፡

4/ የክልል አደረጃጀቶች ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ አደረጃጀት ሆኖ በብሔራዊ አደረጃጀት የሚወጡ ፖሊሲዎችን እና የሚተላለፉ ውሳኔዎችን መሰረት በማድረግ የማኅበሩን አላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

5/ የዞን፣ የልዩ ወረዳ፣ የወረዳ እና የቀበሌ አደረጃጀቶች ተጠሪነታቸው ለሚገኙበት ክልል የአደረጃጀት ተዋረድ ሲሆን በሚወጣው ፖሊሲ እና በየደረጃው የሚተላለፈውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ የማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

## 19. የማኅበሩአወቃቀር

የማኅበሩ ብሔራዊ እና ክልላዊ አደረጃጀቶች የሚከተለው ውስጣዊ አወቃቀር ይኖራቸዋል፤

1/ የብሔራዊ አደረጃጀት የሚከተለው ውስጣዊ አወቃቀር ይኖረዋል፡፡

ሀ) ጠቅላላ ጉባዔ፣
ለ) የአስተዳደር ቦርድ እና
ሐ) ብሔራዊ ጽሕፈት ቤት::

2/ የክልል፣ የዞን፣ የልዩ ወረዳ እና ወረዳ እንደ አስፈላጊነቱ በየራሳቸው አደረጃጀት የሚከተለው ውስጣዊአወቃቀርይኖራቸዋል፡፡

ሀ) ጠቅላላ ጉባዔ፣
ለ) የአስተዳደር ቦርድ እና
ሐ) ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት::

3/ ማኅበሩ በቀበሌ ደረጃ እንደአስፈላጊነቱ የቀይ መስቀል ኮሚቴ ሊኖረው ይችላል፡፡

4/ የክልልቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በየጊዜው ማኅበሩ የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች እና የሚያስተላልፋቸውን ውሳኔዎች አፈጻጸም በተመለከተ ለብሔራዊ ጽሕፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

## 20. <u>የማኅበሩ ብሔራዊ ጠቅላላ ጉባዔ አባላት</u>

የብሔራዊ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

1/ የብሔራዊአስተዳደር ቦርዱ ዘጠኝ አባላት፤

2/ ከእያንዳንዱ ክልል ቅርንጫፍ ጠቅላላ ጉባኤ በምርጫ የሚወከሉ አምስት አምስት አባላት፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከሚመረጡ አባላት በተጨማሪ በክልላዊ አደረጃጀቶች ውስጥ ከ100,000 አባላት በላይ ያሏቸው ወረዳዎች፣ ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች ወይም ክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በምርጫ የሚልኳቸው ተጨማሪ አንዳንድአባላት ይኖራሉ፤ ሆኖም ከክልላዊ አደረጃጀቶች የሚመረጡት የጠቅላላጉባዔአባላት ብዛት ከ25 መብለጥ የለበትም፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ ብሄራዊ ጠቅላላ ጉባኤው በሚያወጣው የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡

4/ ከሚከተሉት መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች በሚኒስትር ወይም በከፍተኛ ኃላፊ ደረጃ የሚወክል አንድ ሰው፡

- ሀ) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣
- ለ) የአገር መከላከያ ሚኒስቴር፣
- ሐ) የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣
- መ) የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣
- ሠ) የትምህርት ሚኒስቴር፣
- ረ) የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር፣
- ሰ) የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን፣
- ሸ) የብሔራዊ የመረጃ እና የደህንነት አገልግሎት፣

5/ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ተወካይ፣

6/ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ተወካይ፣

7/ በቀይ መስቀል ብሔራዊ ወጣቶች ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የተመረጡ 3 የቀይ መስቀል ወጣት አባላት፤

8/ የቀይ መስቀል ሠራተኞች ማኅበር ተወካይ፣

9/ በብሄራዊ ቦርዱ የሚጨመሩ ከ 30 የማይበልጡ የቀይ መስቀል አባላት

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3)፣ (7) እና (9) መሰረት የሚመረጡ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት የአገልግሎት ዘመን አራት ዓመት ይሆናል፡፡ ማንኛውም የጠቅላላ ጉባኤ አባል ከሁለት ተከታታይ የአገልግሎት ዘመን በላይ በጠቅላላ ጉባኤ አባልነት መመረጥ አይችልም፡፡ይሁን እንጂ ከላይ የተቀመጠው ድንጋጌ አባሉ ከአንድ የአገልግሎት ዘመን ዕረፍት በኋላ እንደገና ተመርጦ ከማገልገል አያግደውም፡፡

## 21. <u>የብሔራዊ ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>

ብሔራዊ ጠቅላላ ጉባኤው የማኅበሩ ከፍተኛ አካል ሲሆን የሚከተሉትሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1/ የአስተዳደር ቦርድ አባላትን መምረጥ፤

2/ የማኅበሩን ፖሊሲ ማውጣት ወይም ማጽደቅ፤

3/ ለአስተዳደር ቦርዱ አስፈላጊውን አጠቃላይ የፖሊሲ መመሪያ መስጠትና አፈጻጸሙንም መከታተል፣

4/ የአስተዳደር ቦርዱ የሚያቀርበውን የማኅበሩን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ ዕቅድና ጥቅል በጀት ማፅደቅ፣

5/ የአስተዳደር ቦርዱንና የኦዲተሮችን ሪፖርት መርምሮ ማጽደቅ፣

6/ በአስተዳደር ቦርዱ የተወሰኑ በበጀት ያልተመለከቱ ከፍተኛና አስቸኳይ የድንገተኛ አደጋ ወጭዎች ካሉ መርምሮ ማጽደቅ፣

7/ የአስተዳደር ቦርዱ በሚያቀርበው ሃሣብ መሠረት የአባልነት ክፍያንና የክልል ጽ/ቤቶች ለማኅበሩ ብሔራዊ ጽ/ቤት የሚያደርጉትን የመዋጮ መጠን መወሰን፣

8/ የአስተዳደር ቦርዱ በሚያቀርበው ሃሣብ መሠረት ከማኅበሩ መርሆች ጋር በተዛመደ መልኩ ከፍተኛ ሰብዓዊ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ላበረከቱ የክብር አባልነትን እንዲሁም የማኅበሩን ከፍተኛ ሜዳይና ሽልማት ሊያገኙ የሚገባቸውን ተሸላሚዎች መወሰን፣

9/ ለሁለት ዓመታት የሚያገለግል የማኅበሩን የውጭ ኦዲተር መሰየም፣

10/ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ የማኅበሩን ቻርተር ማሻሻልና እንዲጸድቅ ለመንግሥት ማቅረብ፣

11/ የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት እና ስለአስተዳደር ቦርድ አባላት ምርጫ ደንብ ማጽደቅ፤

12/ የማኅበሩን የብሄራዊ ጽሕፈት ቤት እና በክልላዊ አደረጃጀት ስር የተዋቀሩትን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች አወቃቀር፣ ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ በአስተዳደር ቦርዱ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን ደንብ ማጽደቅ፤

13/ ማኅበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

14/ የማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ያከናውናል።

## 22. <u>የብሔራዊ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ</u>

1/ የብሔራዊ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ በየሁለት ዓመቱ የማኅበሩ የሁለተኛው በጀት ዓመት በተፈጸመ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል።

2/ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ የጠቅላላ ጉባዔ ልዩ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።

3/ ልዩ ጠቅላላ ጉባዔ ሊጠራ የሚችለው፣

ሀ) በአስተዳደር ቦርዱ ውሳኔ፣ ወይም

ለ) ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት መካከል በአንድ ሦስተኛው ድምጽ ሲጠየቅ፣ ወይም

ሐ) ግማሽ ወይም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የክልል የአስተዳደር ቦርዶች በውሳኔያቸው ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ ከጠየቁ ነው።

4/ የጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ስብሰባ የሚደረግ መሆኑን የሚያመለክት ማናቸውም ማስታወቂያ፣ የአስተዳደር ቦርዱና የኦዲተሮች ዘገባዎች፣ እንዲሁም ጉባዔው የሚነጋገርባቸው ሌሎች ጉዳዮች ዝርዝር ስብሰባው ከሚጀመርበት አንድ ወር አስቀድሞ ለጉባዔው አባላት መላክ ይኖርባቸዋል።

5/ የጠቅላላ ጉባዔ ልዩ ስብሰባ የሚነጋገርባቸው ጉዳዮች ዝርዝር ስብሰባው ከሚጀመርበት ጊዜ አሥራ አምስት ቀን አስቀድሞ ለጉባዔው አባላት እንዲላኩ ይደረጋል።

## 23. <u>የብሔራዊጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>

1/ የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ በማኅበሩ ፕሬዚዳንት ይመራል።

2/ በዚህ ቻርተር በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፤

ሀ) ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

ለ) ማንኛውንም ውሳኔ ማሳለፍ የሚቻለው በጉባዔው ከተገኙት እና ድምጽ ከሰጡት መካከል በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤

ሐ) ድምጽ እኩል ለዕኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት ምልዓተ ጉባዔ ያልተገኘ እንደሆነ ጉባዔው በአሥራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ይጠራል። በሁለተኛ ጥሪ የተሰበሰበው ጉባዔ በተገኙ አባላት የድምጽ ብልጫ ውሳኔዎችን ሊያሳልፍ ይችላል።

4/ እያንዳንዱ የጠቅላላ ጉባዔ አባል አንድ ድምጽ ብቻ ይኖረዋል።

5/ የጉባዔው ውይይቶችና ውሳኔዎች ጉባኤው በመረጣቸው ዘጋቢዎች ተይዘው በፕሬዚዳንቱና በዘጋቢዎች ይፈረማሉ።

## 24. <u>የብሔራዊ የአስተዳደር ቦርድ አባላት</u>

1/ የማኅበሩ የአስተዳደር ቦርድ በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ ዘጠኝ አባላት ይኖሩታል፤ ከአባላቱ አንዱ ከወጣቶች የሚመረጥ ተወካይ ይሆናል።

2/ የአስተዳደር ቦርድ አባላት ምርጫ የፆታ፣የልምድ እና የሙያ ስብጥርን መሰረት ያደረገ ይሆናል።

3/ የአስተዳደር ቦርድ አባላት የሚመረጡት ለብሔራዊ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ተጠርተው ከተገኙ አባላት ነው። ይሁን እንጂ ለጠቅላላ ጉባኤው ተጠርተው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መገኘት ያልቻሉትን እና በጠቅላላው ጉባኤ የሚሰጣቸውን ኃላፊነት እንደሚወጡ ፈቃደኝነታቸውን በጽሁፍ ወይ በሌላ መንገድ ያረጋገጡ አባላትን በአስተዳደር ቦርድ አባልነት ሊመርጥ ይችላል።

4/ የማኅበሩ ዋና ጸሐፊ ድምጽ የማይሰጥ አባልና ጸሐፊ ይሆናል።

5/ አስተዳደር ቦርድ አባላቱ ከሙያቸው ወይም ከቀደመ ታሪካቸው የተነሳ የማህበሩን ሃላፊነት በአግባቡ እንዳይወጡ ከሚያደርጋቸው የጥቅም ግጭት ነጻ መሆን አለባቸው።

6/ አስተዳደር ቦርድ አባላቱ ኃላፊነታቸውን በሚወጡበት ጊዜ እና በሥራ እንቅስቃሴያቸው ሁሉ ለማኅበሩ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። የብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ አባላት በፖለቲካ ድርጅት ወይም በመንግስት መዋቅር ውስጥ ከፍተኛ ኃላፊነት ከተሰጣቸው ከአስተዳደር ቦርድ አባልነቱ ይለቃሉ ወይም ይህ የተሰጣቸው ኃፊነት ከማኅበሩ የገለልተኝነት መርህ ጋር እንደማይጋጭ ማረጋገጫ ይሰጣሉ።

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተገለጸው ገደብ ቢኖርም በማናቸውም ሁኔታ በአስተዳደር ቦርዱ ውስጥ ከሶስት በላይ በፖለቲካ ድርጅት ወይም በመንግስት መዋቅር ውስጥ ከፍተኛ ኃላፊነት ያላቸው አባላት ሊኖሩ አይችሉም።

## 25. <u>የብሔራዊአስተዳደርቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን</u>

1/ የብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለአራት ዓመታት ይሆናል፤ሆኖም አንድ አባል የአገልግሎት ዘመኑን ከጨረሰ በኂላ እንደገና ተመርጦ ማገልገል ይችላል።

2/ አንድ አባል በተመሳሳይ ደረጃ ከሁለት ተከታታይ የአገልግሎት ዘመን በላይ ሊያገለግል አይችልም፤ ይሁን እንጂ ይህ ድንጋጌ አባሉ ከአንድ የምርጫ ዘመን በኂላ እንደገና ተመርጦ ከማገልገል አያግደውም።

## 26. <u>የብሔራዊ የአስተዳደርቦርድ ሥልጣንና ተግባር</u>

የአስተዳደር ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1/ ከአባላቱ መካከል የማኅበሩን ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ዓቃቤ ንዋይ መምረጥና በጠቅላላ ጉባዔው ማስጸደቅ፤

2/ ቦርዱ የሚያቋቁማቸውን የአማካሪ ኮሚቴዎችን ሰብሳቢዎች መምረጥ፤

3/ በዚህ ቻርተር አንቀጽ 11 የተመለከተው የማኅበሩ ተግባር በሚገባ መከናወኑን ማረጋገጥ፣

4/ የማኅበሩ ብሔራዊ ጽ/ቤት ሥራ በሚገባ መከናወኑን መከታተልና መቆጣጠር፤

5/ የማኅበሩን ዋና ጸሐፊ መምረጥና መመደብ፣ አጠቃላይ የስራ መመሪያ መስጠት፣ ኃላፊነቱን የማይወጣ ሆኖ ሲገኝ ከሥራ ማሰናበት፤

6/ በማኅበሩብሔራዊ ጽ/ቤት በቀጥታ ለዋና ጸሐፊ ተጠሪ በሆኑ የሥራ መደቦች ላይ የሚመደቡትን የሥራ ኃላፊዎች ምርጫ ማጽደቅ፤

7/ በተሰየመው ኦዲተር የተመረመረውን የሂሣብ ሪፖርት በየሁለት ዓመት ለጠቅላላ ጉባዔ ማቅረብ፤

8/ የማኅበሩን የሁለት ዓመታት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርትና የተከታዩን የሁለት ዓመታት የሥራ ዕቅድና ጥቅል በጀት ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ ማስጸደቅ፤

9/ በጠቅላላ ጉባኤው በጸደቀው ጥቅል በጀት መሰረት የማኅበሩን አመታዊ የስራ ዕቅድ እና ዝርዝር በጀት ማጽደቅ፤

10/ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ በማይደረግበት ጊዜ የጉባዔውን ውሳኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ ውሣኔ መስጠትና በሚቀጥለው ስብሰባ አቅርቦ ማስጸደቅ፤

11/ የማኅበሩ የፋይናንስና ንብረት አማካሪ ኮሚቴ በሚያቀርበው ሃሣብ መሠረት የማኅበሩን የመጠባበቂያና ሌሎች ልዩ ልዩ ሂሣቦች ማቋቋምና አጠቃቀማቸውን መወሰን፤

12/ የማኅበሩ መሠረታዊ መርሆች በየደረጃው በሚገባ መከበራቸውንና በሥራ መተርጐማቸውን ማረጋገጥ፤

13/ የማኅበሩን አንድነት እና ህልውና አደጋ ላይ የሚጥልድርጊት ሲፈጸም፣ የማኅበሩ መሰረታዊ መርሆችና ዓላማ በየትኛውም የማኅበሩ እርከን ተጥሷል ወይም አልተከበረም ብሎ ሲያምን አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ የመውሰድና አፈጻጸሙንም ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ማቅረብ፤

14/ የአባልነትን ክፍያ መጠን፣ ክልሎች ለብሔራዊ ጽሕፈት ቤት፣ ዞኖች/ልዩ ወረዳዎች ለክልል እንዲሁም ወረዳዎችለዞን ስለሚያደርጉት የመዋጮ መጠን አጥንቶ ለጠቅላላ ጉባዔው የውሳኔ ኃሳብ ማቅረብ፣ ሲጸድቅም አፈጻጸሙን መከታተል እና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፤

15/ ስለውጭ እርዳታ አስፈላጊነትና አጠቃቀም መወሰን፣ለማኅበሩ ከቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴ አካላት ውጪ የሚደረግለትን እርዳታ መፍቀድ፤

16/ የቀይ መስቀልና የቀይ ጨረቃ ዓለምአቀፍ ድርጅቶችና እህት ማኅበራት አስፈላጊ ሲሆን ከማኅበሩ ጋር በኅብረት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰሩ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመነጋገር ፈቃድ መስጠት፤

17/ ለክብር አባልነት የሚያበቁ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ፤ የክብር አባልነት የሚሰጣቸው ሰዎችን ለጠቅላላ ጉባዔው ማቅረብና ማስጸደቅ፣

18/ ከቦርድ አባላት መካከል እስከ ሶስት አባላት በአባልነት ሊቀጥሉ ያልቻሉ እንደሆነ እስከ ተከታዩ ጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ስብሰባ ድረስ የሚያገለግሉ ሌሎች አባላትን መርጦ መተካት፣

19/ ጊዜያዊ ወይም ቋሚ አማካሪ ኮሚቴዎችን እንደአስፈላጊነቱ ማቋቋም፣ በበላይነት መምራት፣ ተግባራቸውንም መወሰን፤

20/ በማኅበሩ እንቅስቃሴዎች የላቀ አስተዋጽኦ ላደረጉ የማኅበሩ አባላት፣ በጎ ፈቃደኞች እና ሰራተኞች ሽልማት መስጠት፤

21/ የጠቅላላ ጉባዔውን የስብሰባ ጊዜ፣ ቦታና አጀንዳ መወሰን፤

22/ ማኅበሩን በመወከል የውጭ ግንኙነት ማድረግ፤

23/ በጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፤

24/ የማኅበሩን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ሌሎች ተያያዥ ሥልጣንና ተግባራትይኖሩታል።

## ክፍል አራት

## የማኅበሩ የሥራ መሪዎች ሥልጣንና ተግባር

### 27. ጠቅላላ

የማኅበሩ የሥራ መሪዎች ተግባራቸውን የሚያከናውኑት በዚህ ቻርተርና በማኅበሩ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል። ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ምንጊዜም ቢሆን የማኅበሩን ጥቅም ማስቀደም አለባቸው።

### 28. የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

የማኅበሩ ፕሬዚዳንት የማኅበሩ የበላይ ኃላፊ ሲሆን የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1/ ማህበሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 እና 11 የተቀመጡትን አላማ እና ተግባራት መወጣቱን እየተከታተለ ለብሔራዊ አስተዳደር ቦርድ ሪፖርት ያቀርባል፤

2/ የብሔራዊ ጠቅላላ ጉባዔውንና የብሔራዊ አስተዳደር ቦርድ ስብሰባዎችን በሊቀመንበርነት ይመራል፤

3/ የማኅበሩን አጠቃላይ ሁኔታ በተመለከተ ለጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርት ያቀርባል፣

4/ የማኅበሩን የተለያዩ ክፍሎች ስራ ያስተባብራል፤

5/ የብሔራዊ ጠቅላላ ጉባዔውና የብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

6/ የአስተዳደር ቦርዱ ሊሰበሰብ በማይችልበት ጊዜ ከዋናው ጽ/ቤት በሚቀርቡ አስቸኳይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤ ውሳኔዎቹንም በተከታዩ የቦርድ ስብሰባ አቅርቦ ያስጸድቃል፤

7/ የአስተዳደር ቦርዱን ወክሎ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤

8/ በአስተዳደር ቦርድ እና ጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል።

## 29. <u>የማኅበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የማኅበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1/ ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሰራል፣

2/ በፕሬዚዳንቱ እና በአስተዳደር ቦርዱ በተለይ የሚሰጠውን ተግባር ያከናውናል።

## 30. <u>የማኅበሩ ዓቃቤ ንዋይ ሥልጣንና ተግባር</u>

የማኅበሩ ዓቃቤ ንዋይ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1/ የማኅበሩን የፋይናንስና ንብረት አማካሪ ኮሚቴን በሊቀመንበርነት ይመራል።

2/ የማኅበሩን የንብረት እና የፋይናንስ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የአፈጻጸሙንም ሪፖርት በየስድስት ወሩ ለብሔራዊ አስተዳደር ቦርድ ያቀርባል።

## 31. <u>የማኅበሩ ዋና ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

ዋና ፀሐፊው የማኅበሩ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ሲሆንተጠሪነቱ ለአስተዳደር ቦርድ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1/ የማኅበሩን ብሔራዊ ጽሕፈት ቤት በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

2/ በክልላዊ አደረጃጀት ስር በሚገኙ ቅርንጫፍጽህፈት ቤቶች የሚገኙ ሰራተኞች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት መተዳደራቸውን ያረጋግጣል፤ ጉድለት ሲያገኝ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

3/ በክልላዊ አደረጃጀት ስር በሚገኙ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ያለው የማኅበሩ ስራ በማኅበሩ ሕግና መመሪያ መሰረት እየተፈጸመ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በየወቅቱም ለብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፤

4/ ከአስተዳደር ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የማኅበሩን ሒሳብ ያንቀሳቅሳል፤

5/ በማኅበሩ የፋይናንስ እና የግዢ መመሪያዎች መሰረት ለማኅበሩ ስራ የሚያስፈልጉ የፋይናንስ እና የግዢ ውሳኔዎችን ይሰጣል፤

6/ በዚህ ቻርተርና በማኅበሩ የውስጥ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የማኅበሩን ልዩ ልዩ ተግባራት በሚገባ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

7/ የማኅበሩን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ይቻል ዘንድ የብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት ከሌሎች የቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴ አካላት ጋር እንዲሁም አግባብነት ካላቸው ሀገራዊና ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል፣ ከእነዚህ አካላት ጋር ስለሚደረጉ ግንኙነቶች እና ስለተገኘው ውጤት በየወቅቱ ለአስተዳደር ቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፤

8/ ለሥራ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ጊዜያዊና ቋሚ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፤

9/ የማኅበሩን የሥራ ዕቅድና ፕሮግራም እንደዚሁም በጀት አዘጋጅቶ ለአስተዳደር ቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

10/ የብሔራዊ ጠቅላላ ጉባዔውንና የአስተዳደር ቦርዱን ውሳኔዎች ሥራ ላይ ያውላል፤

11/ በየዓመቱና እንደአስፈላጊነቱ በየወቅቱ የማኅበሩን የሂሣብ መግለጫዎች ለአስተዳደር ቦርዱ ያቀርባል፤

12/ ከፕሬዚዳንቱ ጋር በመመካከር የብሔራዊ አስተዳደር ቦርድ ስብሰባዎችን አጀንዳ አዘጋጅቶ ከአስፈላጊ ሠነዶችና መረጃዎች ጋር ለእያንዳንዱ አባል ይልካል፤

13/ ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለዋና ጸሐፊ በሆኑ የማኅበሩ ዋና ጽ/ቤት የሥራ መደቦች ላይ የሚመደቡትን ኃላፊዎች በውድድርበመምረጥ ለብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፤

14/ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎችን ቅጥር እና ስንብት ሒደት በብሔራዊ ጽ/ቤቱ ድጋፍ በክልል አስተዳደር ቦርድ በኩል እንዲፈጸም ያደርጋል፣ በክልሉ አስተዳደር ቦርድ በኩል የቅርንጫፍ ኃላፊዎችን ቅጥር እና ስንብት አስመልክቶ የሚቀርብለትን የውሳኔ ኃሳብ መርምሮ ያጸድቃል፤

15/ የማኅበሩ አማካሪ ኮሚቴዎች ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋል ወይም ሌላ ሰው ይወክላል፤

16/ በብሔራዊ ጽ/ቤት የሚገኘውን የማኅበሩን ቋሚ ንብረት እና ገንዘብ ያስተዳድራል፣ እንዲሁም በክልል ጽ/ቤቶች የሚገኘውን የማኅበሩንቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ገንዘብን ጨምሮ በማኅበሩ ደንብና መመሪያ መሰረት መተዳደሩን ያረጋግጣል፣ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘውም የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

17/ የብሔራዊ ጽ/ቤት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

18/ የማኅበሩን መሰረታዊ መርሆች ያከብራል፣ በሰራተኞች መከበራቸውንም ይከታተላል፤

19/ ለዚህ ቻርተር አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑትን የውስጥ ደንቦችና መመሪያዎች ለቦርዱ በማቅረብ ያስጸድቃል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤

20/ ከብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ማኀበሩን ይወክላል፤

21/ ማኀበሩን ወክሎ ውል ይዋዋላል፣ይከሳል፣ይከሰሳል ወይም አስፈላጊውን ውክልና ይሰጣል፤

22/ ከብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ እና ከፕሬዚደንቱየሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለማኀበሩ ገቢና የሂሣብ መግለጫዎች

### 32. የማኀበሩ የገቢ ምንጮች

የማኀበሩ የገቢ ምንጮች ከማኀበሩ መርሆች ጋር የማይጋጩ፣ ማኀበሩ መርሆቹን እንዲጥስ የማያስገድዱ እና ተግባርና ሃላፊነቱን ከመወጣት የማያግዱት ሆነው፤ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፣

1/ ከአባልነት ክፍያ፣

2/ ከውርስ፣ ከስጦታ እና ከዕርዳታ ከሚገኝ ገንዘብና ንብረት፣

3/ ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች፣

4/ ከመንግሥት ከሚሰጥ ጠቅላላ ወይም የፕሮግራም ድጐማ፣

5/ ከአምቡላንስና ከሌሎች አገልግሎቶች፣

6/ ዓላማውንለማስፈጸም የማህበሩን መሠረታዊ መርሆችበመጠበቅከሚሰሩ የገቢ ማስገኛ እና የንግድ ሥራዎች ከሚገኝ ገቢ

7/ ከሌሎች የገቢ ምንጮች፡፡

### 33. ከግብር እና ቀረጥ ነጻ ስለመሆን

1/ ማኀበሩ ዓላማውን ለማስፈጸም ከውጪ በግዥም ሆነ በስጦታ በሚያስመጣቸው ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ እና በገቢ ዕቃዎች ላይ ከሚጣሉ ታክሶች ነጻ ይሆናል፡፡

2/ በሌሎች ህጎች ለማኀበሩ የተሰጡ መብቶች እና ጥቅሞች እንደተጠበቁ ሆነው ማኀበሩ ከአባልነት ክፍያ፣ በውርስ ከሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት፣ ከስጦታ፣

ከመንግስት ድጎማ እና ከአምቡላንስ አገልግሎት በሚያገኘው ገቢ ላይ ግብር ከመክፈል ነፃ ይሆናል፡፡

## 34. የማኅበሩ የበጀት ዓመት

የማኅበሩ የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ይሆናል

## 35. ስለሂሳብ መዛግብት

1/ ማኅበሩ ገቢዎቹን በግልጽነት እና በተጠያቂነት መርህ መሰረት ያስተዳድራል፡፡

2/ ማኅበሩ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

## 36. ስለ ኦዲት

1/ የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ እስከ 6 ወር ድረስ በኦዲተር የተረጋገጠ የሂሣብ ሪፖርት ለብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ ይቀርባል፡፡

2/ በየሁለት ዓመቱ በውጪ ኦዲተር የተረጋገጠ የሂሣብ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔው ይቀርባል፡፡

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 37. የቻርተሩ መሻሻል

1/ ይህ ቻርተር ከብሔራዊ ጠቅላላ ጉባዔ አባላት ሁለት ሦስተኛው ተገኝተው ከዚህ ውስጥ ሁለት ሦስተኛው የተስማሙበት ሃሣብ ለመንግሥት ቀርቦ ሲፈቀድ ሊሻሻል ይችላል፡፡

2/ ማኅበሩ ቻርተሩን ማሻሻል ሲፈልግ በአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ እና በአለም አቀፍ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ፌዴሬሽን የብሔራዊ ማኅበራትን ቻርተር ለመመርመር ለተቋቋመው የጋራ ኮሚሽን ያሳውቃል፣ የሚሰጡትንም አስተያየቶች ግንዛቤ ውስጥ ያስገባል፡፡

## 38. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በዚህ ቻርተር መሠረት ምርጫና የሥራ ድልድል እስከሚደረግ ድረስ በሥራ ላይ ያሉ የማኅበሩ ተመራጮች ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

## 39. የውስጥ ደንብ የማውጣት ሥልጣን

በዚህ ቻርተር በሌሎች አንቀጾች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ ለዚህ ቻርተር አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑትን የውስጥ ደንቦችን ለማውጣት ይችላል፡፡

## 40. ስለ ተሻሩ ሕጎች

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር የተሻሻለው ቻርተር አዋጅ ቁጥር 153/1991 ተሽሮ በዚህ ቻርተር ተተክቷል፡፡

## 41. ቻርተሩ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ቻርተር በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ------------------/2009 ዓ.ም

ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚደንት